

**ተመልከት ፡ ዓላማህን ፣**
**ተከተል ፡ አለቃህን ፤**

## ተበታትናችሁ ፡ በስደት፡ ኗሪና፡ ኢትዮጵያኖች፡ ወገኖቸ ፤

ክቡራትና ፡ ክቡራን ፡ ወገኖቸ ፡ ሆይ!

ዓለማትን ፡ በማካለል ፡ በየቦታው ፡ ተበታትነን ፡ በመኖራችንና ፡ ነብሳችን ፡ በመሰንበቷ ፡ አይደንቀኝም ። የሚደንቀኝ ፡ ግን ፡ ያንን ፡ ሁሉ ፡ ችጋር ፡ አሳልፈን ፡ ወጥተን ፡ ሐሣበ ፡ ብትን ፡ መሆናችን ፡ ነው ። የሰሜን ፡ አመሪካ ፡ ሰብዓዊ ፡ መብታችንን ፡ አስተውለን ፡ በጥሞና ፡ ለመወያየት ፡ ተስኖናል ። በየዜና ፡ ማሰራጫው ፡ የምናየውንና ፡ የምናነብበውን፡ ሳናሥብበት ፡ በችኮላ፡ እንገነፍላለን ። መናገርና ፡ መጻፋችንን ፡ እንጂ ፡ ውጤቱ ፡ ለምንፈልገው ፡ ዓላማ ፡ ጠቃሚነቱን ፡ ማመዛዘን ፡ የተሳነን ፡ ይመስለኛል ። በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ የእንጀራ ፡ አገራችንን ፡ አኗኗር ፡ ለመቋቋም ፡ ያለብን፡ ግፊት፡ ከፍተኛ ፡ መሆኑ ፡ አይዘነጋም ። እናም ፣ ጥለነው ፡ ለመጣነው ፡ ትግል ፡ ደጋፊ ፡ ለመሆን ፡ የምናከናውነው ፡ ተግባር ፡ እርካታ ፡ ሰጥቶናል ። ሆኖም ፣ ለትውልድ ፡ አገራችን ፡ ትግል ፡ የመሳተፉ ፡ መብታችን ፡ ገደብ ፡ አለው ። የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፡ መሪውን ፡ መርጧል ። ሰላማዊ ፡ ትግሉንም ፡ ዐውጇል ። የሕዝባዊ ፡ ድምፅ ፡ እንቅስቃሴ፡ ድርጅቱንም፡ **ቅንጅት** ፡ ብሎ ፣ "**ቅንጅት** ፡ መንፈስ፡ ነው ፣ **መሪያችን ፡ ኃይሉ** ፡ ነው" ። የተሰኘውን ፡ አዝማቹን ፡ እየዘመረ ፡ በመትመም ፡ ላይ ፡ ነው ። ስለዚህ ፣ መሪና ፡ ተመሪ ፡ የድርጅቱን ፡ ሕጋዊ ፡ ውስጠ ፡ ደንብ ፡ ድንጋጌ ፡ አክብሮና ፡ ተከባብሮ ፡ በኀብረት ፡ መሥራትን ፡ ይጠይቃል ።

ሰሞኑን ፡ በተከበሩት ፡ መምህር ፡ መስፍን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ በተናኜው ፡ ኑዛዜ ፡ ደጋፊና ፡ ተቃዋሚ ፡ አግኝተዋል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፣ ስሜታቸውን ፡ ፊት ፡ ለፊት፡ በመግለጽ ፡ ታዋቂው ፡ መስፍንን ፡ ግዜ ፡ እየጣላቸው ፡ የሄደ ፡ ይመስላል ። በየዜና ፡ ማሰራጫውና ፡ ከእርሳቸውም ፡ እንዳገኜሁት ፡ ማረጋገጫ ፤ ስለ ፡ ቅንጅ



ት ፡ ላዕላይ ፡ መማክርትና ፡ መሪዎች ፡ ሰሜን ፡ አመሪካ ፡ ከመጡ ፡ በኋላ ፡ የመከፋፈል ፡ ችግር ፡ ቀድሞም ፡ እንደነበረ ፡ ዐዋቂ ፡ መሆናቸውን ፡ ያረጋግጣል ። ተንኮለኞቹና ፡ ሥልጣን ፡ ጥመኞቹም ፡ እርሳቸው ፡ ባቋቋሙት ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ ወይዘሮ ፡ ብርቱካን ፡ ሚደቅሳን ፡ ድጋፍ ፡ እንዲሰጣት ፡ ያስተላለፉት ፡ ቃለ ፡ ኑዛዜ ፣ ለተንኮሉ ፡ አበረታች ፡ ሊያሰኛቸው ፡ ይችላል ። ወሳኙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መሆኑን ፡ እያወቁ ፡ አወዛጋቢ ፡ መልእክት ፡ ማስተላለፋቸው ፡ ግራ ፡ ያጋባል ። ከዚያ ፡ በፊትም ፡ ልደቱ ፡ አያሌውንና ፡ ዶር ፡ ተብየው ፡ ብርሃኑ ፡ ነጋን፡ ያበረታቱ ፡ እንደነበሩና፡ የሁለቱን ፡ ሰዎች ፡ ጋጠ ፡ ወጥነት፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲከተሉ ፡ ይምከሯቸው ፡ ተብለው ፡ ነበረ ። ይኸም ፡ አባባል ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ውስጥ ፡ በነበሩት ፡ አባል ፡ ቃለ ፡ መጠየቅ ፡ መልስ ፡ ተመሥክሯል። ወደ ፡ ኋላም ፡ ከነአካቴው ፡ የመሠረቱትን ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ድርጅት ፡ ትተውላቸው ፡ በገለልተኛነት ፡ ተቀመጡ ። ታዲያ ፣ እርሳቸው ፡ ይመሯቸውና ፡ ያስተምሯቸው ፡ የነበሩትን ፡ ጋጠ ፡ ወጦች ፡ ተሰላችተው ፤ የቅንጅት ፡ መሪውን ፡ "ኃላፊነቱን ፡ ምን ፡ እንደሆነ፡ አለመረዳቱን ፡ ነው ፡ የሚያሳየኝ" ። ብሎ ፡ መፍረዱ ፡ ግዜውና ፡ ተገቢ ፡ ነወይ? ። ሥልጣን ፡ ይዘው ፡ ሳለ ፡ ሥልጣን ፡ ጥመኛ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ ከምኑ ፡ ላይ ፡ ነው? ። ያውም ፡ አልፈልገውም ፡ ለሚሉትና፡ የሀገራቸው ፡ ጉዳይ፡ ጭምር ፡ በሽታ ፡ ሆኖ ፡ ለሚያሰቃያቸው ።

ወገኖቸ ፡ ሆይ!........እንደሳቸው ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ የሚወረውሩት ፡ ትንታግ ፡ ከተቀጣጠለ ፡ መብረጃ ፡ ስለሌለው ፡ አሁኑኑ ፡ እንዲታሠብበት ፡ አደራ ፡ እላለሁ ። ክቡር ፡ መምህር ፡ መስፍን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፣ የከፍተኛ ፡ ተቋም ፡ ተማሪዎችን ፡ በመቀስቀስና ፡ ተቃውሞ ፡ በማሰማት ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ። በኃላፊነት ፡ ከመምራት ፡ ግን ፡ እስተ ፡ አሁን ፡ በመሸሽ ፡ ላይ ፡ አሉ ። የወሎን ፡ ድርቅ ፡ አስመልክቶ ፡ በተቀዳሚ ፡ ያስተዋወቁት ፡ ዜና ፤ ከተማሪው ፡ ወደ፡ መምህሩ ፣ ከመምህሩ ፡ ወደ፡ ሕዝቡ ፣ ከሕዝቡ፡ ወደ ፡ ወታደሩ ፡ ተዛምቶ ፡ የንጉሣዊ ፡ አገዛዙን ፡ አስገርስሷል ። በደርግ ፡ ግዜም ፡ የታሠሩትን ፡ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ፡ መርምሮ፡ ለማጣራት ፡ የተመረጡት ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ እሳቸውና ፡ በረከት ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡ ነበሩ ። የደርግ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ውሳኔውን ፡ ለማፋጠን ፡ የምርመራቸውን፡ ውጤት፡ እንዲያስታውቋቸው፡ ሲጠይቋቸው፤ ግዜ ፡ የማትሰጡን ፡ ከሆነ ፦ "ፈረሱም ፡ ይኸው ። ሜዳውም ፡ ይኸው ።

ምን ፡ ትጠብቃላችሁ" ። ብለው ፡ ስለነበረ ፤ ከባለቤቱ ፡ ጋራ ፡ ተጣ
ልቶ ፡ ሲደበድባት ፡ ያዩ ፡ ሽማግሌ ፦ "ወዳጄ ፡ መፍታት ፡ ሳለ ፡
መምታት?" እንዳሉት ፡ ሳይሆን ፡ ታሥረው ፡ አገራቸውን ፡ ሊያገለ
ግሉ፣ ተተኪውን ፡ ትውልድ ፡ ሊያስተምሩ ፡ የሚችሉትን ፡ ዕውቅ ፡
የሥራ ፡ ልምድና ፡ ትምህርት ፡ ያካበቱ ፡ ወገኖቻችንን ፡ ያለ ፡ ፍር
ድ ፡ አስረሸናቸው ። የአሁኑም ፡ ኑዛዜአቸው ፡ በጣም ፡ አደገኛና ፡
ጥለውት፡ ለወጡት ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ድርጅታቸው ፡ አድሎትኛ ፡
ስለሆነ ፡ ከውጭና ፡ ከውስጥ ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሊአ
ወግዘው ፡ የሚገባ ፡ መስሎ ፡ ይታየኛል ። ኑዛዜ ፡ ሲባል ፡ የመጨረ
ሻ ፡ አምላክ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ቃለ ፡ ንሥሐ ፡ ነበረ ። እና ፡ ሰው ፡
የሚታረቅበትን ፡ ምክር ፡ ማዘጋጃ ፡ እንጂ ፡ "እኔ ፡ ከሞትኩ ፡ ሰር
ዶ ፡ አይብቀል" ። እንደሚሉት ፡ ዓይነት ፡ ትቶ ፡ ለማለፍ ፡ መሞከ
ሩ ፣ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የሠሩትን ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ አፍራሽ ፡ ይሆ
ናል ።

"ከአጋም ፡ የተጠጋ ፡ ቁልቋል ፡ ዘለዓለም ፡ ሲያለቅስ ፡ ይኖ
ራል" ። ነውና ፡ ቁልቋሉን ፡ ለማዳን ፡ ሕዝብ ፡ መክሮ ፡ አጋሙን ፡
መመንጠር ፡ ነው ። በቀስተ ፡ ደመናም ፡ ለቅንጅት ፡ እንቅፋት ፡ የ
ሚሆኑትን ፡ ቦርቡሮ ፡ አውጥቶ ፡ መቆጣጠር ፡ ያስፈልጋል ። ቀድ
ሞውንም ፡ "እጸድቅ ፡ ብየ ፡ ባዝላት ፡ ተንጠልጥላ ፡ ቀረችን" ፡ አ
ሥቦ ፡ የክቡር፡ መኃንዲስ ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ ድርጅት ፡ ብዛት ፡ ስ
ለነበረው ፡ ውስጣዊ ፡ ስምምነት ፡ መፈራረምና፡ የትግራይ ፡ ዲቃላ ፡
ወያኔን ፡ ወኪሎች ፡ የመቆጣጠር ፡ ግዴታ ፡ መሆን ፡ ነበረበት ።

"ታሪክ ፡ እራሱን ፡ ይደግማል" ። እንደሚሉት ፡ ደርግ ፡ ሲ
ቋቋም ፡ ማንም ፡ ባለሥልጣን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እንዳይወጣ ፡
ተወስኖ ፡ ነበረ ። ቆየት ፡ ብሎ ፡ ግን ፡ የ፲ ፡ አለቃ ፡ ለገሠ ፡ አስፋ
ው ፡ ወደ ፡ ሩሲያ ፡ ደርሶ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ጭካኔ ፡ ገነነ ። አ
ሁንም ፡ የብሃኑ ፡ ነጋን ፡ ከትግራይ ፡ ዲቃላ ፡ ወያኔ ፡ ተግባቢ ፡ ከ
ውጭ ፡ አገር ፡ ዜጐች ፡ ጋራ ፡ ለማሾክሾክ ፡ ከቅንጅት ፡ መሪው ፡
ተለይቷል ። ከስብሰባ ፡ እያቋረጠ ፡ የመውጣት ፡ ስልቱም ፡ የጓደኛ
ው ፡ የመለስ ፡ ለገሠ ፡ ዜናዊ፡ ግልባጭ ፡ ነው። ለዚህም ፡ ማስረጃ ፡
አውስትራሊያ ፡ ኗሪ ፡ የሆኑትና ፡ የቀድሞው ፡ የወያኔ ፡ ገንዘብ ፡ ያ
ዥም ፡ ከመሥራቾችም ፡ አንዱ ፡ አቶ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ የሰጡት
ን ፡ ቃለ ፡ መጠየቅ ፡ መልስ ፡ ያዳምጧል ። "ወያኔ ፡ እንደገባ፦ ይ
ላሉ ፡ አቶ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፣ አቶ ፡ መለስ ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ኤር
ትራ ፡ ሄዶ ፡ ለሦስት ፡ ሳምንታት ፡ ያህል ፡ ቆይቶና ፡ መመሪያ ፡
ተሰጥቶት ፡ ተመለሰ" ። እንግዲህ ፡ ጓደኛው ፡ ብርሃኑ ፡ ነጋስ ፡ ዓ



ይናችሁ ፡ ጉድ ፡ ይመልከት ፡ እያለን ፡ አይደለም ፡ ወይ? መድኅን
ና ፡ ኢሕአፓ ፡ መሣሪያ ፡ እናንሣ ፡ ብለዋልና ፡ ጸጥታን ፡ ያደፈርሳ
ሉ ፡ ተብለው ፡ አልነበረም ፡ ወይ? ብርሃኑ ፡ ሲናገር ፡ የወያኔ ፡ ዲ
ቃሎች ፡ ዝም ፡ ያሉበት ፡ ምክንያት ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ምክር ፡
ስላለበት ፡ አይመስላችሁም? ሥልጣን ፡ ጥመኛው ፡ ብርሃኑ ፡ ነጋን ፡
መወገዝ ፡ አይገባውም ፡ የምንል ፡ ካለን ፡ ቂሎች ፡ ነን ። ኧረ ፡ ለ
መሆኑ ፡ ብርሃኑ ፡ ነጋ ፡ የአመሪካ ፡ ዜግነት ፡ ያለው ፡ አይደለም ፡
ወይ? ከሆነስ ፡ እንዴት ፡ የመዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ከንቲባ ፡ ሆኖ ፡ ሊሠራ፡
ቻለ? ቀስተ ፡ ደመናና ፡ ቅንጅትስ ፡ አመሪካዊነቱን ፡ በተመለከተ ፡
ምን ፡ የወሰዱት ፡ እርምጃ ፡ ነበረ? አለ? ይኖራል? በነገራችን ፡ ላይ
ም ፦ የኤፍሬም ፡ ይሥሐቅን ፡ በአዲስ ፡ ድምፅ ፡ ቃለ ፡ መጠየቅ ፡
መልስ ፡ ብታዳምጡ ፣ "እኔማ ፡ ምኞቴ፡ ከዚህ ፡ ሽምግልና፡ በኋላ ፡
ውጭ ፡ ሄጄ ፡ እየዞርኩ ፡ ያልተቀራረቡትን ፡ ማቀራረብ፡ የወደፊት ፡
ዕቅዴ ፡ ነው" ። ይላል ። እንዳለውም ፡ ለነብርሃኑ ፡ ነጋ ፡ ለማመቻ
ቸት ፡ ያልተመካከረ ፡ ይመስላችኋል? አመሪካ ፡ ከገቡ ፡ በኋላስ ፡
መሪአቸው ፡ ክቡር ፡ መኃንዲስ ፡ ኃይሉ ፡ ሻውልን ፡ በማግለል ፡ ዋ
ሽንግተን ፡ ዲ . ሲ . ሜትሮ ፡ አካባቢ ፡ በነበረው ፡ ስብሰባ ፡ በነኤ
ፍሬም ፡ ውስጠ ፡ ምሥጢር ፡ ደባ ፡ የለበትም ፡ ማለት ፡ ይቻል ፡
ይሆን? እኔ ፡ የጠረጠርኩበት ፡ ምክንያቴም ፡ ከወይዘሪት ፡ ሜሮን ፡
አሃዱ ፡ ሣቡሬና ፡ ከመምህር ፡ ዓለማዬሁ ፡ ገብረ፡ ማርያም ፡ ጋራ ፡
ቀጠሮ ፡ ነበራቸው ። ኤች ፡ አርር ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ሦስትን ፡ ለተቃ
ወሙ ፡ ይሁዳዊ ፡ አመሪካውያን ፣ ሕጉ ፡ የሚለውን ፡ ለማስረዳት ፡
ተስማምተው ፡ የነበሩ፡ መሆናቸውን ፡ አሰምተውን፡ ስለነበረ፡ ነው ።
ከዚያ ፡ ስብሰባ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ የቅንጅት ፡ መልክተኞች ፡ መከፋፈ
ል ፡ ለይቶለት ፡ ይፋ ፡ የወጣ ።

ወይዘሮ ፡ ብርቱካን ፡ ሚደቅሳም ፡ በኋላ ፡ በር ፡ በግርግር ፡
ግዜ ፡ ቅንጅት ፡ ውስጥ ፡ የገባች ፡ እንጂ ፡ ተመርጣ ፡ ስላልሆነ ፡
መጣራት ፡ አለበት ። ሊወገዙ ፡ የሚገባቸው ፡ ድርጊቶችም ፡ ፈጽማ
ለች። <u>ለምሣሌ፦</u> ፩ኛ ፡ በስብሰባ ፡ ከተጠሩ ፡ በኋላ ፡ የታሠርነው ፡
ብቻ ፡ ነን ፡ መወያየት ፡ የሚገባን ፡ ብላ፡ በመከፋፈል ፡ ድርጅቱን ፡
ለጉዳት ፡ ዳርጋለች። ፪ኛ ፡ በአመሪካ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ታሠሩ
ት ፡ ሰዎች ፡ ብዛት ፡ ስትጠየቅ ፡ መቶ ፡ ብላ ፡ መልሳለች ። ይህ ፡
አመላለሷም ፡ የቀስተ ፡ ደመናን ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አጠቃ
ላይ ፡ ሁኔታ ፡ ግድ ፡ የሌላት ፡ የሥልጣን ፡ ጥመኛ ፡ መሆኗን ፡ ያስ
ረዳኛል ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የመሪትነት ፡ ችሎታዋ ፡ አርቆ ፡

አሣቢነት : ስለ : እሚጐድላት : አገርና : ወገን : ከመጐዳቱ : በፊት : ሕዝብ : አሥቦ : ሊያግዳት : ይገባል ። ወጣቱንም : እናደራጃለን : በሚል : የምትመራው : ቡድን : አሳሳች : ጐዳናን : ይዞ : በመራመድ : ላይ : ነው ። በአሥተሳሰባቸውም : ከነመኃንዲስ : ኃይሉ : ሻውል : ጋራ : ተቃራኒውን : ስለ : እሚያሥቡ : አደገኞች : ናቸው ። ሚኔሶታ : ሄደው : ብርቱካን : ያደረገችውና : መሥመሩን : የሳተ : ትግሬዎችን : ይቅርታ : ጥየቃ ፣ <u>**በቅጥፈት**</u> : “ዕቃ : ወደ : ቀበሌ ፣ ትግሬ : ወደ : መቀሌ” ። በቅንጅት : አባል : ተብሏል : ለተባለው : በተቃራኒ : አንብቢ : ተብላ : የተሰጣት : መሆኗን : ማሠብ : ባያዳግተኝም ፣ አገርና : ወገንን : ጐጅ : በመሆኑ : አዝኛለሁ ። ተበሳጭቻለሁ። ጠበቂትና: ዳኝት : ነበረች: ከምትባል : ሴት : የምጠብቀው: ይኽን : አልነበረም! ። እንደዚህች: ያለችውን : ሴት : ነው : መምህር : መስፍን : ወልደ : ማርያም: “በሥልጣን : ጥመኞች : አጣብቂኝ : ነው : ያለችና : እርዷት” : የሚሉን ። አጣብቂኝን : ካነሱ : አይቀር : እንደ : እሚትፈልጉት : ማዘዝ : ለሚሹት : በእርሳቸውና : በብርሃኑ: ነጋ : መካከል : እንደነበርች : ያሣሥበኛል። የአለምርጫ : መግባቷ : ምንን : ያመለክታል!? ። ይኽንንም : መኃንዲስ : ኃይሉ : ሻውል : እርምጃ : የሚወስዱበት : ጉዳይ : ይሆናል ። የሥልጣን : ጥመኛነቷን : ደግሞ : ግጥሟን : ማጤኑ : ይበቃል ። በዚህ : ዕድሜአቸው : መምህር : መስፍን : ወ/ማርያም : ሕዝብ : የመረጠውን : መሪ : የሥልጣን : ጥመኛ : ማለቱ : ነውረኛነትን : ያሳየኛል ።

“ሰው : ማለት : ሰው : በጠፋበት : ግዜ : ሰው : ሆኖ : መገኘት : ነው” ። <u>በመኃንዲስ : ኃይሉ : ሻውል ።</u>

በየባላገሩ : እየዞሩ : ሕዝቡን : ተስፋና : ብርታት : እንዲኖረው : በሚያበረታቱበት : ወቅት : ተንቀሳቃሽ : ምሥላቸውንና : ንግግራቸውን : ሳዳምጥ : ከተማርኩት ፦ ሕዝብ : መብቱን : እንዲያስከብር : ከመምከራቸው : በላይ: ፍርሃትን : አውልቆ : ድፍረትን: እንዲቀዳጁ: ያደፋፍሩ : ነበሩ። ስለ : ኢትዮጵያ : አገራችንም : ምጣኔ : ሀብት: ውድቀት : መሻሻል : አስተሣሠባቸውና : ከማጥም : ለማውጣት: ያላቸውን : ጥረት: ሣሥብ : አንድ : የአመሪካ : መሪ : ትዝ : ስላሉኝ ፤ እንዲያውም: አመሪካ : መኃንዲስ : ኃይሉ : ሻውልን : የሚደግፍ : ታሪክ : አለውና : እንሆ!..... ክቡር : አቶ : ፍራንክሊን : ዴላኖ : ሮዝቬልት : የተባበሩ: አመሪካ : መንግሥታትን : ለመምራት : በ፲፱፻፳፬ : ዓመተ : ምህረት : ተመረጡ ። በዓመቱ :



፲፱፻፳፭ : የግድያ : ሙከራ : ተደርጐባቸው : ሕይወታቸው : ተረፈ። ግዜው : የሁለተኛው : ዓለም : ጦርነት : መጀመሪያ : ስለ : ነበረ : ከፍተኛ : የምጣኔ : ሀብት : ቀውስ : ነበረባቸው ። በቆራጥነታቸው : ግን : የአሜሪካ : ሕዝብ : በተስፋ : በርትቶ: እንዲሠራ : በማበረታታት : አገራቸውን : ከውድቀት : አዳኑና : ዝነኛ : ሆነው : ታወቁ ። ከዚያም : ወደ : ግራ : አመለካከት : ያላቸው : ምክትላቸውን፦ ክቡር : አቶ : ሄንሪ : ዋላስን : ሽረው : የሕግ : መወሰኛ : አባል: የሆኑትን : ክቡር: አቶ : ሔሪ : ኤስ : ትሩማንን: ተክተው : ከምርጥ : አማካሪዎቻቸው : ጋራ : በተከታታይ : ዐራት : ግዜ : ተመርጠው: ለዐሥራ : ሁለት : ዓመታት : እንደ : መሩ : በድንገት : ናላቸው : ውስጥ : ደም : ፈስሶ : ቢሯቸው : ውስጥ : ዐረፉ። ታዲያ : እኒያ : የተከበሩ : መሪ : በተሽከርካሪ : ወንበር : በሕዝብ : ፊት : ሲሽከረከሩ : ላለመታየት : ተጠንቃቂ : ሰው : ነበሩ ።

“He was elected in 1932. Assuming the Presidency at depth of the Great Depression, Franklin Delano Roosevelt helped the American people regain faith in themselves. He brought hope as he promised prompt vigorous action, and asserted his Inagural address, “the only thing we have to fear is fear itself”. The “country asks for action, and action now. Our greatest primary task is to put people to work”. Though dearly ailing, he was leading the nation at the time of war. He used a wheelchair, but he was careful never to be seen in it in public. In February 1933, Roosevelt escaped an assassination attempt. He dumped his left-leaning vice president, Henry Wallace, in favour of Senater Harry S. Truman, and together they won the race. He brought in a team of first –rate thinkers and drew on their ideas as he saw fit”.

እናም : ገና : በሕክምና : ላይ : ያሉት : ብርቱው : መሪያችን : ክቡር : መኃንዲስ : ኃይሉ : ሻውልን : እኒ : ብርሃኑ : ጨለመ : ክፉ : ሲያሥቡባቸው : መታየቱ : ቅጥ : ያጣ : አረመኔነት: ነው ። ሆኖም : እኒ : ጨለማው : በመኃለጣቸው : የኢትዮጵያ : አምላክ : አገረና : ወገን : ወዳጁን : መሪ : አኃልጦ : የማይሰጥ : ለመሆኑ : ማረጋገጫ : ነውና : ኀብረታዊ : ጥረታችንን : እንቀጥል ።

የእግዚአብሕር : እርዳታ : ተጨምሮበት : ኢትዮጵያና : ቅንጅት : በመኃንዲስ : ኃይሉ : ሻውል : መሪነት: ያሸንፋሉ። አሜን።



ሰውዓለም : ጐሹ ፣ ካናዳ ።

ጥቅምት : ፲፬ : ቀን : ፳፻ : ዓመተ : ምሕረት ።